# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐቡሊክ
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በውጭ አገር ስለሚሠሩ ኢትዮጵያውያን
## የሥራ ሥምሪትና ደህንነት አጠባበቅ እና ወደ ኢትዮጵያ
## መጥተው ተቀጥረው ስለሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች
## የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ አስመልክቶ
## ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ላይ የተከናወነ
## የክዋኔ ኦዲት ረቂቅ ሪፖርት

ታኅሣሥ 2004

አዲስ አበባ

# ማውጫ


መግቢያ ........................................ 1

የሚኒስቴር መ/ቤቱ አመሰራረት ........................................ 1

የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሥልጣንና ተግባሮች ........................................ 2

የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አደረጃጀት ........................................ 2

የሰው ኃይል ........................................ 3

የፋይናንስ ምንጭ ........................................ 3

የኦዲቱ ዓላማ ........................................ 3

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ ........................................ 4

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት ........................................ 4

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........................................ 4

የሥራ ሂደት መግለጫ ........................................ 5

ወደ ውጭ አገር ለሚሄዱ ኢትዮጵያውያን ውል የማጽደቅ የሥራ ሂደት ........................................ 5

ለውጭ አገር ዜጎች አዲስ የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ የሥራ ሂደት ........................................ 5

ክፍል ሁለት ........................................ 6

ግኝቶች ........................................ 6

ወደ ውጭ አገር ሠራተኛ የሚልኩ ኤጀንሲዎች የላኳቸውን ሠራተኞች ለሥራ በሄዱበት አገር ኤምባሲ ወይንም ቆንስላ ጽ/ቤት አቅርበው ማስመዝገባቸውንና የሥራ ፈቃድ ማግኘታቸው መረጋገጡን በተመለከተ። ........................................ 7

የሥራ ውል ሲታደስና ሲሻሻል በአቀራቢያው ያለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲያውቁት መደረጉን በተመለከተ። 8

በውጭ አገር ሥራንና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ላይ የሚደረግ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓትን በተመለከተ። ........................................ 9

በውጭ አገር ለሥራ የተሰማሩ ሠራተኞች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ አቤቱታዎች አፈታትን በተመለከተ። ........................................ 10

በውጭ አገር ሥራ የሚሰማራ ሠራተኛ በውጭ አገር ለሚሰማራበት የሥራ መስክ ተገቢ ሥልጠና ያለው መሆኑን በተመለከተ። ........................................ 11

ለሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ። ........................................ 12

ወደ ውጭ ለሥራ የሚሄዱ ሠራተኞች መክፈል የሚገባቸውን የክፍያ ሂሣብ ብቻ የከፈሉ መሆኑን በተመለከተ። ........................................ 13

ኤጀንሲዎች ያገኙትን የውጭ ምንዛሬ በአገር ውስጥ ባንክ ገቢ ማድረጋቸዉን በተመለከተ። ........................................ 15

የዉጭ ሀገር የሥራ ሥምሪት በጸደቀው የሥራ ውል መሰረት መፈጸሙን ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ። ..15

በዉጭ ሀገር ለሥራ ተሰማርተዉ የሚመለሱ ዜጎች በአገር ውስጥ በተለያየ የሥራ መስክ እንዲሰማሩ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ። ........................................ 16

ለውጭ አገር ሥራ ሥምሪት የተዘጋጀው የሥራ ውል በየዓመቱ መከለሱን በተመለከተ። ........................................ 17

2.2. በሀገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ ሀገር በስራ ተሰማርተዉ ለሚሠሩ ዜጎች የሥራ ሥምሪት የተደራጀ
ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ የተዘረጋና ዉጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ በተመለከተ፣ .................................................................18

የሥራ ፈቃድ የተሰጣቸው የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ሥምሪት ከሚያደርጉበት ክልል ጋር ሚኒስቴር መ/ቤቱ
የዘረጋው የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓትን በተመለከተ፣ ..................................................................................19

ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተቀጥረው ለሚሰሩ የውጭ አገር ዜጎች የፈቃድ አሰጣጥ ና የሥራ ስምሪት
ቀልጣፋና ፍትሀዊ መሆኑን በተመለከተ፣ ...........................................................................................................21

ለውጭ ዜጎች የሥራ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ሥራው በኢትዮጵያውያን አለመሸፈኑ መረጋገጡን በተመለከተ፣ ..............................22

ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ሲሰጥ ለተባለው የሥራ መስክ ተገቢው ሙያ ያላቸው መሆኑን መረጋገጡን በተመለከተ፣ .............23

ተቀጥረው የሚመጡ የውጭ ዜጋ ሠራተኞች በሚሰሩበት ቦታ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን የቴክኒክ ወይም
የክህሎት ሽግግር የሚያደርጉበት ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣ ...................................................................24

ክፍል ሦስት ........................................................................................................................................26

የመደምደሚያ ሀሳቦች ...........................................................................................................................26

ክፍል አራት ........................................................................................................................................29

የማሻሻያ ሀሳቦች ................................................................................................................................29

አባሪ 1 ...............................................................................................................................................33

**በውጭ አገር ስለሚሠሩ ኢትዮጵያውያን የሥራ ሥምሪትና ደህንነት አጠባበቅ እና ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተቀጥረው ስለሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ አስመልክቶ በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ረቂቅ ሪፖርት**

# ክፍል አንድ

## 1.1 መግቢያ

1. የአንድ አገር ኢኮኖሚን ለማንቀሳቀስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉት ዋነኛ ተዋንያን መካከል ሠራተኞችና አሠሪዎቻቸው ይጠቀሳሉ፡፡ በሠራተኞችና አሠሪዎቻቸው መካከል ያለው ግንኙነት በምርታማነት ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ በሥራ ቦታ ላይ የሠራተኞችን የሙያ ደህንነት እና ጤንነታቸውን በተመለከተ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ በተጨማሪም ዜጎች በተለያየ ሙያ ላይ ከአገር ውጭ ተቀጥረው ሲሄዱ ለሥራ ተሰማርተው በሄዱበት አገር ደህንታቸውና ጤንነታቸው የተረጋገጠ መሆኑን ለማጣራት ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡
2. በአገር ውስጥ ባለሙያ ሊሸፈን የሚችል የሥራ መስክም ለዜጎች ቅድሚያ እየተሰጠ ሊሸፈን አለመቻሉ ሲረጋገጥ ብቻ የሌላ አገር ዜጋ የሆኑ ባለሙያዎች ሊቀጠሩ ይገባል፡፡ የተቀጠሩትም ባለሙያዎች የቴክኒክ ክህሎታቸውን ለአገር ውስጥ ባለሙያዎች የሚያስተላልፉበት ስልትም መነደፍ አለበት፡፡
3. የውጭ አገር ሠራተኞች ቅጥርን በተመለከተና የኢትዮጵያውያን በውጭ አገር የሥራ ስምሪትን በተመለከተ ያለውን ሥራ በፌዴራል ደረጃ እንዲሠራ ኃላፊነት የተሰጠው የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፡፡

**የሚኒስቴር መ/ቤቱ አመሰራረት**

4. የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አሁን ያለውን አደረጃጀት ከመያዙ በፊት በ1949 ዓ.ም. "ሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር" በሚል ስያሜ በትዕዛዝ ቁጥር 15/1949 ማኅበራዊና ኢኪኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት ታስቦ የተቋቋመ መ/ቤት ነበር፡፡ ከአስር ዓመታት በኋላ የመ/ቤቱ ስያሜ የኅዝባዊ ኑሮ እድገትና የማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር በትዕዛዝ ቁጥር 46/1958 ተቀይሮ የማህበራዊ ደህንነትና የአሠሪና ሠራተኛን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ጭምር ሲያከናዉን ቆይቷል፡፡ በመቀጠልም ቀደም ስል ሲያከናውን የቆየውን የህዝባዊ ኑሮ እድገት ሥራን በመተው በአሁኑ ጊዜ የሚጠራበትን "የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚ/ር የሚለዉን

ስያሜ በአዋጅ ቁጥር 127/1969 እንዲይዝ ተደረገ፡፡ በ1980 ዓ.ም. የተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት በአዋጅ ቁጥር 8/1980 ተሻሽሎአል፡፡

5. በ1987 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት ሲመሰረት በአዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 20 መሰረት የፌዴራል መ/ቤት ሆኖ እንደገና ተቋቁሟል፡፡ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት እንደገናም በአዋጅ ቁጥር 471/1998 እና በአዋጅ ቁጥር 691/2003 ተሻሽሎአል፡፡

### የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሥልጣንና ተግባሮች

6. የሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 691/2003 መሰረት ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባሮች መካከል፡-
    - ቀልጣፋና ፍትሀዊ የሥራ ሥምሪት አገልግሎት ሊኖር የሚችልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
    - ለዉጭ አገር ሰዎች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ይወስናል፣ ፍቃድ ይሰጣል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይቆጣጠራል፣
    - የኢትዮጵያውያን የውጭ አገር የሥራ ስምሪት አገልግሎትን ይቆጣጠራል፣
    - በሀገሪቱ ውስጥ መደበኛ በሆነና መደበኛ ባልሆነ ሥራ ላይ ስለተሰማራዉና በሥራ አጥነት ስለሚገኘው የሰው ኃይልና ስለሙያ አመዳደብ ጥናት ያደርጋል፣ የሥራ ገበያ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል ያሰራጫል፣
    - ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች ውስጥ የሚገኙ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅቶችን የሚመለከቱ የሠራተኛ ማኅበራትንና የህብረት ስምምነቶችን ይመዘግባል፣ በነዚሁ ድርጅቶች ውስጥ የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር አገልግሎት ተግባሮችን ያከናዉናል፣ በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን በስምምነት ለመጨረስ የማስማማት አገልግሎት ይሰጣል፣

    የሚሉት ይገኙበታል፡፡

### የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አደረጃጀት

7. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተፈቀደለት አዲስ መዋቅር መሰረት አንድ ሚኒስትር፣ ሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች፣ አንድ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ፣ አንድ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ፣ አስራ አንድ ዳይሬክቶሬቶች እና አንድ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል አሉት፡፡

**የሰው ኃይል**

8. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በታህሳስ 11/ 2004 ዓ.ም ላይ 141 ወንድ እና 155 ሴት ሠራተኞች በድምሩ 296 ቋሚ ሠራተኞች ነበሩት፡

**የፋይናንስ ምንጭ**

9. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠዉን ኃላፊነት ለመወጣትና በዕቅድ የያዛቸውን ሥራዎች ለማስፈጸም የሚያስፈልገዉን በጀት በአብዛኛው ከመንግሥት በየአመቱ የሚመደብለት መደበኛ በጀት ሲሆን በተጨማሪ ከተለያዩ ለጋሽ ሀገራት እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ያገኛል፡፡ ዝርዝሩ በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ ተመልክቷል፡፡

| በጀት ዓመት | የተገኘ የገንዘብ መጠን | | ሥራ ላይ የዋለ የገንዘብ መጠን | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከመደበኛ በጀት | ከለጋሽ አካላት | ከመደበኛ በጀት | | ከለጋሽ አካላት | |
| | | | ብር | በመቶኛ | ብር | በመቶኛ |
| 2001 | 8,017,885.66 | 711,389.17 | 7,832,022.40 | 98% | 476,609.10 | 67% |
| 2002 | 9,429,298.20 | 2,379,823.00 | 8,993,672.42 | 95% | 1,613,451.67 | 68% |
| 2003 | 6,713,080.48 | 1,344,682.23 | 6,456,935.02 | 96% | 808,472.47 | 60% |

**የኦዲቱ ዓላማ**

10. የኦዲቱ ዓላማ ዜጎች በተለያየ ሙያ ላይ ከአገር ውጭ ተቀጥረው ሲሄዱ ለሥራ ተሰማርተው በሄዱበት አገር ደህንነታቸውና ጤንነታቸው የተጠበቀ መሆኑንና በአገር ውስጥ ሊሸፈን የሚችል የሥራ መስክም ለዜጎች ቅድሚያ እየተሰጠ ሊሸፈን አለመቻሉ ሲረጋገጥ ብቻ የሌላ አገር ዜጋ የሆኑ ባለሙያዎች መቀጠራቸውን እንደዚሁም የተቀጠሩትም ባለሙያዎች የቴክኒክ ክህሎታቸውን ለአገር ውስጥ ባለሙያዎች የሚያስተላልፉበት ስልትም የተዘረጋ እና ሥራ ላይ የዋለ መሆኑን በመገምገም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ላይ የሚታዩ ድክመቶች ካሉ መንስዔዎቻቸውን በመለየት የማሻሻያ ሃሳብ ለማቅረብ ነው፡፡

**የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ**

11. ከላይ የተገለጸውን የኦዲት ዓላማ ለማሳካት ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፡፡ እነሱም
    1. በውጭ ሀገር ስለሚሰሩ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች የሥራ ስምሪት ደህንነት አጠባበቅ ቀልጣፋና ፍትሐዊ መሆኑን ማረጋገጥ
    2. በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር በሥራ ተሰማርተው ለሚሰሩ ዜጎች የሥራ ስምሪት የተደራጀ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ መኖሩንና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ እና
    3. ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተቀጥረው ስለሚሰሩ የውጭ አገር ዜጎች የፈቃድ አሰጣጥና የሥራ ስምሪት ቀልጣፋና ፍትሀዊ መሆኑን ማረጋገጥ፣

    የሚሉ ናቸው፡፡

**የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት**

12. ለዝርዝር ኦዲቱ ለተመረጡት ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች 38 መመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁ ሲሆን የተዘጋጁትንም መመዘኛ መስፈርቶች ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በማቅረብ ተገቢ ለመሆናቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

**የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ**

13. ዝርዝር ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2001-2003 ያሉትን የሦስት በጀት ዓመታት እና የ2004 የመጀመሪያ ሩብ ዓመትን የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡ የዝርዝር ኦዲቱ በዋናኛነት የተከናወነው በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፡፡
14. ለኦዲቱ የሚረዱ መረጃዎች ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ ጽ/ቤት፣ ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት፣ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን ጽ/ቤት፣ በናሙና በተመረጡ በውጭ አገር የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጄንሲ ቢሮዎች በመገኘት ከሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ጋር ቃለ መጠይቅ እና የተለያዩ ሰነዶችን በመከለስ መረጃ ተሰብስቧል፡፡
15. እንዲሁም በናሙና የተመረጡ ወደ 72 ለሚሆኑ ውጭ አገር ለሥራ ለሚሄዱ ሠራተኞችም መጠይቅ ቀርቧል፡፡ በናሙና ላልተካተቱት ቀሪ ክልሎች ለሚገኙ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤቶች መጠይቆች (survey questionnaires) ተልኳል፡፡ ነገር ግን ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀ ድረስ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሠራተኛና ማኅበራዊ

ጉዳይ ኤጀንሲ እና ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት በቀር ለተላከው መጠይቅ መልስ አልመጣም፡፡

## የሥራ ሂደት መግለጫ

### ወደ ውጭ አገር ለሚሄዱ ኢትዮጵያውያን ውል የማጽደቅ የሥራ ሂደት

16. በውጭ አገር ሥራ መገኘቱን የሚገልጽ ሰነድ ከግለሰብ ወይም ከሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጄንሲ አማካኝነት ለውጭ አገር ሥራ ፈቃድ አገልግሎት ኤክስፐርት ይቀርባል፣ ኤክሰፐርቱ ሰነዱን ከመረመረ በኋላ ሰነዱ የተሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥ ሠራተኞቹ የቅድመ ጉዞ ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፣ የቅድመ ጉዞ ሥልጠናውን እንዳጠናቀቁ ሠራተኞቹ የሥራ ውሉን ይፈራረማሉ፣ ውሉም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ይጸድቃል፡፡ የሠራተኞቹ መረጃ በመ/ቤቱ ዳታ ቤዝ ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል፣ የውሉን መጽደቅንም ሠራተኞቹን ሥራ ላገናኘው አገናኝ ኤጄንሲም በደብዳቤ እዲያውቀው ይደረጋል፣ በመጨረሻም ሁሉም ሰነድ ሥራውን በሰራው የሥራ ፈቃድ ኤክስፐርት ተፈርሞ ወደ መዝገብ ቤት ይላካል፡፡

### ለውጭ አገር ዜጎች አዲስ የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ የሥራ ሂደት

17. በአገር ውስጥ ለመሥራት የሥራ ፈቃድ የሚፈልግ የውጭ አገር ዜጋ የሥራ ፈቃድ እንዲሰጠው እራሱ ወይንም ሠራተኛውን ሊቀጥረው በፈለገው ድርጅት አማካኝነት ጥያቄው ለሥራ ፈቃድ ሠራተኛው ይቀርባል፣ የቀረቡት መረጃዎች በሥራ ፈቃድ ሠራተኛው ተመርምረው የተሟሉ ሆነው ከተገኙ ፈቃድ ጠያቂው አስፈላጊውን ክፍያ እንዲፈጽም የገንዘብ ክፍያ መክፈያ ፎርም ለአመልካቹ ይሰጠዋል፣ ፎርሙን በመሙላት ለሂሳብ ሠራተኛው ሲያቀርብ የሂሳብ ሠራተኛው የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ በማዘጋጀት ገንዘቡን ይቀበላል፣ ደረሰኙንም ለከፋዩ ይሰጣል፣ ለሠራተኛውም የሥራ ፈቃድ ደብተር ተዘጋጅቶ ይሰጠዋል፣ የሥራ ፈቃድ ለውጭ አገር ዜጋው የተሰጠ መሆኑን እንዲያውቁት ደብዳቤ፣ ለዜግነትና ኢሚግሬሽን መምሪያ፣ ለቀጣሪው ድርጅት እና ለፌዴራል ፖሊስ ተዘጋጅቶ ይላካል፣ መረጃው ወደ ዳታ ቤዝ ይገባል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### 2.1 በውጭ ሀገር ስለሚሠሩ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች የሥራ ስምሪት ደህንነት አጠባበቅ ቀልጣፋና ፍትሐዊ መሆኑን ማረጋገጥ

**በውጭ ሀገር ተቀጥረው ስለሚሠሩ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች የቅጥር ውልን ማጽደቅን በተመለከተ፣**

18. ለሥራ ወደ ውጭ አገር የሚሄድ ሠራተኛ የሥራ ውል በአሠሪው ተፈርሞ እና አሠሪው በሚገኝበት አገር በሚገኝ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ቀርቦ ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ በኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ የጸደቀው ውል በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ትክክለኛነቱ ከተጣራ በኋላ የሥራ ውሉ ለሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ቀርቦ መጽደቅ አለበት፡፡
19. ይሁን እንጂ በናሙና ከታዩት ወደ ኩዌት፣ ሳውድ አረቢያ እና የተባበሩት አረብ ኢምሬት (ዱባይ) ለመሄድ የተዘጋጁ ሠራተኞች የሥራ ውል ውስጥ ወደ ሳውዲ አረቢያ የሚሄዱ ሠራተኞች የሥራ ውል በቀጣሪው የማይፈረም፣ ሳውዲ አረቢያ ባለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ቀርቦ ውሉ እንደማይጸድቅ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ የሥራ ውሉ የሚሞላውም ሆነ የቀጣሪው ፊርማ ቦታ ላይ የሚፈረመው በኤጀንሲዎች መሆኑ ታውቋል፡፡ በቀጣሪው ያልተፈረመ እና በኢትዮጵያ ኤምባሲ/ ቆንስላ ያልተረጋገጠ ውል በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደሚጸድቅ ተረጋግጧል፡፡
20. በኦዲቱ ወቅት በናሙና መጠይቅ ከቀረበላቸው የውጭ አገር ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ውስጥ አንድ የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ አንድ ዜጋ ያለአሰሪ ፊርማና ካለ ኤምባሲ ማረጋገጫ ከአገር ቢወጣ አሰሪው ፊርሞ ባልተቀበለው ውል ተጠያቂ ማድረግ ስለማይቻል ኤጀንሲው እራሱን ለተወሰነ ጊዜ ከዚሁ ሥራ ለማግልል ማሰቡን በመግለጽ የሣውድ አረቢያ የሥራ ውል /ኢትዮጵያ ኤምባሲ/ ቆንስላ ጽ/ቤት እንዲጸድቅ እንዲደረግ በጽሁፍ በ27/02/04 በቁጥር ተ/ኤም/20085/04 የተጻፈ ደብዳቤ ለሚ/ር መ/ቤቱ ማቅረቡ በኦዲቱ ወቅት ታይቷል፡፡

21. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ ከሳዑዲ አረቢያ በግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች አማካይነት የሚቀርቡ የሥራ ውሎችን በተመለከተ ሀገሩ ሰፊ በመሆኑ ምክንያት የኢትዮጵያ ቆንጽላ ጽ/ቤቶች በሁለት ቦታ (በሪያድ እና በጄዳ) ብቻ ስለሚገኙ አሠሪዎች በቆንጽላ ጽ/ቤት ተገኝተው የሥራ ውሎችን ለመፈረም ከቦታው ርቀት አንጻር አመቺ ባለመሆኑ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ለኢትዮጵያ ቆንጽላ እና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በማሳወቃቸው የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች ጉዳዩን በጋራ ተመልክተውት ከሥራ ሥምሪቱ አኳያ ሳውዲ ሰፊ ገበያ ያለው ሀገር መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት የሥራ ውሎች በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጸድቀው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲረጋገጡ ስምምነት ላይ በመደረሱና በመወሰኑ ምክንያት በዚህ መልኩ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን መልስ ቢሰጡም ለውጭ ጉዳይ ሚ/ር ያሳወቁበትም ሆነ ሚኒስቴር መ/ቤቱና ውጭ ጉዳይ ሚ/ር የተስማሙበት ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

22. በአዋጁ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባወጣው መመሪያ መሰረት ህጉን ባልተከተለ መንገድ በአሠሪው ያልተፈረመና በኤምባሲ ያልጸደቀ ውል በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተቀባይነት ማግኘቱ ለሥራ በሄዱ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች ላይ ችግር ቢፈጠር፣ መብታቸውን ለማስጠበቅ እንዲቻል ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከመፍጠሩም በላይ ለሕገ-ወጥ አሰራር በር ይከፍታል፡፡

**ወደ ውጭ አገር ሠራተኛ የሚልኩ ኤጀንሲዎች የላኳቸውን ሠራተኞች ለሥራ በሄዱበት አገር ኤምባሲ ወይንም ቆንስላ ጽ/ቤት አቅርበው ማስመዝገባቸውንና የሥራ ፈቃድ ማግኘታቸው መረጋገጡን በተመለከተ፣**

23. ለሥራ ሠራተኞችን ወደ ውጭ የሚልኩ በውጭ አገር ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች የላኩዋቸው ሠራተኞች የሥራ ፈቃድ ሊያገኙ ይገባል፡፡ ላኪ ኤጀንሲዎችም በወኪሎቻቸው አማካኝነት ሠራተኞቹ የሥራ ፈቃድ ማግኘታቸውን በሄዱ በ15 ቀናት ውስጥ በአቅራቢያው ወደ ሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ አቅርበው ሊያስመዘግቡ ይገባል፡፡ ሠራተኞቹን ወደ ውጭ የላከ የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲም ሠራተኞቹ የሥራ ፈቃድ ማግኘታቸውን እና በአቅራቢያው ባለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ቀርበው መመዝገባቸውን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡

24. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች በየወሩ ለሚ/ር መ/ቤቱ ተገቢውን ሪፖርት የሚያቀርቡ መሆኑ ሲጣራ፣ የተወሰኑ የሥራና ሠራተኛ አገናኝ

ኤጄንሲዎች ሠራተኞቹን ወደላኩበት አገር ወደሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት የላኳቸውን ሠራተኞ ዝርዝር ብቻ ሪፖርት እንደሚያቀርቡ ነገር ግን የሥራ ፈቃድ ማግኘታቸውን በአዋጁ በተጠቀሰው መሰረት በ15 ቀን ውስጥ እንደማያሳውቁ፣ ቀሪዎቹ የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጄንሲዎች ደግሞ የላኳቸውን ሠራተኞች ዝርዝርም ሆነ የሥራ ፈቃድ ማግኘታቸውን በአቅራቢያው ላለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሪፖርት የማያቀርቡ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው 15 ኤጄንሲዎች ውስጥ ከሁለት ዓመት በላይ የላኳቸውን ሠራተኞች ዝርዝር ሠራተኞቹን በላኩበት አገር ለሚገኝ የኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት ያላሳወቁ እንዳሉ ታውቋል፡፡

25. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በአገር ውስጥ ያሉት የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጄንሲዎች የላኩዋቸውን ሠራተኞች ዝርዝር ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያሳውቁ ቢሆንም ሠራተኞቹ በሚሄዱበት አገር ባለው ኤምባሲ የሌበር አታሼ ባለመኖሩ እንደማያስመዘግቡ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ በየአገሩ የኤጄንሲዎቹ ወኪሎች ስላሉ ወደ ኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት አቅርበው ማስመዝገብ ይቻል ስለነበር የተሰጠውን ምክንያት ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

26. ወደ ውጭ አገር የተላኩ ሠራተኞች በላኪዎቹ ወኪሎች አማካኝነት የሥራ ፈቃድ ማግኘታቸውና በአቅራቢያው ወደሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት አቅርበው አለማስመዘገባቸው እንዲሁም ኤጄንሲዎቹ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት አለማድረጋቸው የተላኩትን ሠራተኞች ደህንነታቸውን ለማስጠበቅም ሆነ ለሚገጥማቸው ችግር በኤምባሲ በኩል አስፈላጊውን እርዳታ ማግኘት እንዳይችሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## የሥራ ውል ሲታደስና ሲሻሻል በአቅራቢያው ያለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲያውቁት መደረጉን በተመለከተ፣

27. ስለ ሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት የወጣ አዋጅ ቁጥር 632/2001 እና አዋጁን ለመተግበር በተዘጋጀው የአፈጻጸም መመሪያ ላይ እንደተገለጸው ቀደም ሲል የተደረገ የሥራ ውል ሲሻሻል እና በአዲስ ሲተካ በሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጄንሲዎች/በወኪሎቻቸው አማካኝነት በአቅራቢያው ለሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይንም ቆንስላ ጽ/ቤት ቀርቦ መጽደቅ አለበት፡፡ የጸደቀውንም የሥራ ውል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲያውቀው ሪፖርት ሊደረግ ይገባል፡፡

28. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ወደ ኩዌት እና ሳውዲ አረቢያ ለሥራ የሄዱ ዜጎች የሥራ ውላቸው ሲታደስ እና ሲሻሻል በአቅራቢያው ወደሚገኝ የኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት ቀርቦ የማይጸድቅና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲያውቀው ሪፖርት እንደማይደረግ ታውቋል፡፡

29. ስለጉዳዩ በናሙና የተመረጡ ኤጀንሲዎች ለቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት መልስ፣ ኩዌት አገር የሚገኙ ሠራተኞች ከሆኑ ቀደም ሲል የተደረገውን የሥራ ውል በአዲስ ለመተካት ወይንም እንደገና ለማሻሻል ሲፈልጉ የተዘጋጀ ፎርም ብቻ በመሙላት ሥራቸውን እንደሚቀጥሉ፣ በሳውድ አረቢያ የሚገኙ ሠራተኞች ደግሞ ቦታ ሲቀይሩ ወይንም ውላቸውን ሲያድሱ በአሠሪዎቻቸው ፈቃድ ብቻ ስለሆነ፣ ሠራተኞቹ ኤጀንሲያቸው እንዲያውቀው ከአደረጉ ብቻ አዲሱን አድራሻ ማወቅ እንደሚቻልና ይህ የተሞላው ፎርምና የተሻሻለ ውል ለላካቸው ኤጀንሲም እንደማይላክና በአቅራቢያው ላለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት ቀርቦ እንደማይጸድቅ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም እንዲያውቀው እንደማይደረግ ገልጸዋል፡፡

30. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በመጀመሪያ ሠራተኞቹ ወደ ውጭ አገር ለሥራ ከመሄዳቸው በፊት በሚሰጠው ገለጻ ወቅት ውላቸውን አድስው ቆይታቸው የሚራዘም ከሆነ በአቅራቢያው ላለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት ማሳወቅ እንዳለባቸው እንደሚነገራቸው፣ ነገር ግን ጉዳዩን ለመከታተል በየአገሩ በሚገኙት ኤምባሲዎች/ቆንስላ ጽ/ቤቶች የሌበር አታሼ እንዲመደብ ከሚመለከታቸው አካለት ጋር ለመነጋገር በዕቅድ መያዛቸውን ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ በየአገሩ የሚገኙ የሥራና ሠራተኛ ኤጀንሲ ወኪሎች ሠራተኞቹን ለማስመዝገብ ሄደው የኢትዮጵያ ኢምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት የሌበር አታሼ ባለመኖሩ ምክንያት መመዝገብም ሆነ መከታተል አልቻልኩም ያለበት ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

31. ለሥራ ወደ ውጭ የተላኩ ዜጎች የሥራ ውላቸው ሲታደስ ወይም ሲሻሻል ውሉ ዜጎችን በማይጎዳ መልኩ መዘጋጀቱን እና ያለውን ለውጥ የኢትዮጵያ ኤምባሲም ሆነ የሚኒስቴር መ/ቤቱ በወቅቱ እንዲያውቁት አለመደረጉ ዜጎች ያሉበትን ሁኔታ ለመረዳትም ሆነ አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

## በውጭ አገር ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ላይ የሚደረግ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓትን በተመለከተ፣

32. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ፈቃድ ለሰጣቸው በውጭ አገር ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ላይ በገቡት ግዴታ መሠረት እየሰሩ ለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚረዳው የክትትልና

የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ በሚደረገው ክትትልና ቁጥጥር አማካኝነት በኤጀንሲዎቹ በኩል በሚታዩ ግድፈቶችና ጉደለቶች ላይ ኤጀንሲዎቹ የእርምት እርምጃ መውሰዳቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ የእርምት እርምጃ በማይወስዱት ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃዳቸውን ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይገባል፡፡

33. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኤጀንሲዎቹን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል፡፡ በክትትሉ ያገኛቸውን ጉድለቶች እና ግድፈቶች እንዲያስተካክሉም ለኤጀንሲዎቹ የሚያሳውቅ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ነገር ግን በሚኒስቴር መ/ቤቱ ኤጀንሲዎቹ የቅድመ ጉዞ ትምህርትና ምክር ለመስጠት የሚያስችል መርጃ መሳሪያ የሌላቸው እንዲያዘጋጁ፣ የተላኩና የተመለሱ ዜጎች መረጃን በተሟላ ሁኔታ እንዲይዙ እና በየጊዜው ወቅታዊ እንዲያደርጉ፣ የሠራተኞች ደህንነትና መብት ሁኔታን አስመልክቶ በየጊዜው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ፣ ለሚቀርቡ አቤቱታዎች ወጥ የሆነ የአቤቱታ የአቀባበልና የአፈታት ስርዓት እንዲዘረጉ፣ የላኳቸውን ዜጎች ዝርዝር በየጊዜው ለኢትዮጵያ ኤምባሲ እንዲያሳውቁ፣ የአገኙትን የውጭ ምንዛሪ በአገር ውስጥ ባንክ ገቢ ስለማድረጋቸው ሪፖርት እንዲያቀርቡ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ከመስጠት በስተቀር የእርምት እርምጃ ባልወሰዱት ላይ ፈቃዳቸውን ያላገደ ብሎም ያልሰረዘ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ሲመልሱ እስካሁን ድረስ ደብዳቤ ከመጻፍ ያለፈ የተወሰደ እርምጃ የሌለ መሆኑንና በቀጣይነት ምን አይነት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት እየተነጋገሩበት መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

34. ሕግና ደንብን አክብረው የማይሰሩና የተገኙባቸውን ጉድለትና ግድፈት በማያሻሽሉት ኤጀንሲዎች ላይ ቀጣይ እርምጃ አለመውሰዱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## በውጭ አገር ለሥራ የተሰማሩ ሠራተኞች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ አቤቱታዎች አፈታትን በተመለከተ፣

35. በውጭ አገር ለሥራ የተሰማሩ ዜጎች እና በቤተሰቦቻቸው የሚቀርቡ አቤቱታዎች አፋጣኝ መልስ የሚያገኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ሥርዓቱም በሥራና ሠራተኛ አገኛኝ ኤጀንሲዎችና ወኪሎቻቸው፣ የኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤትን እና የሚኒስቴር መ/ቤቱ በየደረጃው ለአቤቱታው አፋጣኝ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል መሆን አለበት፡፡ የቀረቡትም አቤቱታዎች እና እንዴት መልስ እንዳገኙ የሚገልጽ መረጃም ተጠናቅሮ ሊያዝ ይገባል፡፡

36. የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አቤቱታ የሚቀበልበትና የሚፈታበት ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ ነገር ግን በናሙና ከተመረጡት 15 የሥራ እና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች የአቤቱታ ፋይል ለመረዳት እንደተቻለው ከውጭ አገር ሥራ ሥምሪት ጋር በተያያዙ ለኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት እና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የቀረቡ ለ181 አቤቱታዎች መልስ ለማግኘታቸው መረጃው ለኦዲት ባለመቅረቡ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

37. የአቤቱታ አቀራረብ እና የመፍትሄ አሰጣጥ አሠራር ምን እንደሚመስል በናሙና ለተመረጡ 15 ኤጀንሲዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ 3ቱ የአቤቱታ መቀበያ ቅጽ በማዘጋጀትና ለወኪላቸው በማሳወቅ ችግሩ በዛ በኩል እንዲፈታ ጥረት እንደሚያደርጉ የገለጹ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ 12ቱ ግን አቤቱታ ሲደርሳቸው ውጭ ወደ ሚገኘው ወኪላቸው በመደወል ችግሩን ለመፍታት እንደሚሞክሩና፣ ከአቅም በላይ ከሆነ ደግሞ በአቅራቢያው ላለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት እንደሚያሳውቁ ገልጸዋል፡፡

38. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ መረጃዎቹ በፋይል ውስጥ ባይያያዙም የቀረቡ አቤቱታዎች በሙሉ መልስ አላገኙም ማለት እንዳልሆነና አብዛኛዎቹ መፍትሔዎች ከኤጀንሲዎችና ከወኪሎቻቸው እንዲሁም ከኢትዮጵያ ኤምባሲ ቆንስላ ጽ/ቤት ጋር በስልክ በመነጋገርና ደብዳቤ በመጻጻፍ እንዲፈታ ስለሚደረግ መሆኑን እንዲሁም ባለው የአቅም ውስንነት ምክንያት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር መረጃዎችና ሪፖርት ልውውጥ የሚደረግበት ሥርዓት ገና ባለመዘርጋቱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

39. ስለሆነም ለቀረቡ አቤቱታዎች የተሰጡ መፍትሔዎች በመረጃ ተደግፈው ካልተያዙ፣ መፍትሔ የተሰጣቸውና ያልተሰጣቸውን መለየት የማይቻልና ተደጋጋሚ ለሆኑ ችግሮች በዘላቂነት መፍትሄ ለማግኘት ሊያስቸግር ይችላል፡፡

## በውጭ አገር ሥራ የሚሰማራ ሠራተኛ በውጭ አገር ለሚሰማራበት የሥራ መስክ ተገቢ ሥልጠና ያለው መሆኑን በተመለከተ፣

40. ለሥራ ወደ ውጭ የሚሄዱ ሠራተኞች የሥራ ውላቸው ከመጽደቁ በፊት ለሚሰማሩበት ሥራ ተገቢው የሙያው ክህሎት እንዳላቸው ወይም ያገኙ መሆናቸውን የውጭ አገር ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች በማረጋገጥ ሠርተፍኬቱን/መረጃውን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ውል ከማጽደቁ በፊት መረጃው መቅረቡንና ትክክለኛነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

41. ኤጀንሲዎቹ የሚልኳቸው ሠራተኞች ተገቢው የሙያ ክህሎት ወይንም ሥልጠና ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የማያቀርቡ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም የማይጠይቅ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

42. ስለጉዳዩ በናሙና የተመረጡ 15 ኤጀንሲዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ሦስቱ ኤጀንሲዎች በመቀናጀት እና በአዲስ አበባ ከኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ በመውሰድ አንድ ማሰልጠኛ በመክፈት የ15 ቀናት ሥልጠና በመስጠት ሠርተፍኬት የሚሰጡ መሆኑን፣ ነገር ግን የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለማይጠይቃቸው የሚልኳቸው ሠራተኞች ውል እንዲጸድቅ ከሚያቀርቡት ማስረጃዎች ጋር ሥልጠናውን የወሰዱ ሠራተኞችን ዝርዝር እንደማያቀርቡ ገልጸዋል፡፡ ቀሪዎቹ 12 ኤጀንሲዎች ሠራተኞቹ ወደ ውጭ ለመሄድ ሦስት እና አራት ቀን ሲቀራቸው ከሚሰጡት አጭር ገለጻ ያለፈ ሥልጠና እንደማይሰጡ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም አንድ የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የማስተማሪያ ማንዋል በማዘጋጀት በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲጸድቅ አቅርቦ እስከአሁን መልስ እንዳላገኘ አስታውቋል፡፡

43. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ፣ ከዚህ በኋላ ወደ ውጭ የሚልኳቸው ሠራተኞች ሥልጠና የወሰዱ እና ሠርተፍኬት ያላቸው ብቻ መሆን እንዳለባቸው ለኤጀንሲዎቹ በደብዳቤ ያሳወቁአቸው መሆኑን፣ ወደ መካከለኛው ምስራቅ የሚሄዱትን ሠራተኞች ለማስተማር የሚያግዝ ሞዴል ቤት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጀ እና መዋቅሩ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሲጸድቅ አስተማሪ ቀጥረው ሞዴል ቤቱ ሥራ እንደሚጀምር ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ለሞዴል ቤቱ አገልግሎት የሚውሉ እቃዎች ከጥር 2003 ጀምሮ ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ገብተው ያለአገልግሎት በአንድ ቤት ውስጥ ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ እንዲሁም ለሲቪል ሰርቪስ ተጻፈ የተባለው መረጃ ስላልቀረበ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

44. ለሚሰማሩበት የሥራ መስክ ተገቢው ክህሎትና ሥልጠና ያላቸውን ሠራተኞች በማረጋገጥ አለመላኩ ሠራተኞቹን በሚሄዱበት አካባቢ ቶሎ እንዳይላመዱ ከማድረጉም በላይ የተሻለ ክፍያ እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለሆነም መ/ቤቱ ያወጣውን መመሪያ ተግባራዊ አለማድረጉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## ለሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ፣

45. የሥራና ሠራተኛ አገናኝነት ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 632/2001 መሠረት ማሟላት የሚገባውን መስፈርት በሚሟላት

ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም መስፈርቱ ሙሉ ለሙሉ መሟላቱን በማረጋገጥ ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ፈቃድ ያገኘ ኤጀንሲም ያለሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ ቅርንጫፍ ቢሮ መክፈት የለበትም፡፡ ኤጀንሲዎቹም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ በማግኘት ቅርንጫፍ በየትኛው ከተማ እንደከፈቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያሳውቁ ይገባል፡፡

46. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከተመረጡ 15 ኤጀንሲዎች የጠቅላላ ጉዳይ ፋይል ለመረዳት እንደተቻለው ኤጀንሲዎቹ ፈቃድ ከማግኘት በፊት ማሟላት ከሚገባቸው መስፈርት ውስጥ ሳያሟሉ ፈቃድ እንደተሰጣቸው ታውቋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የቅድመ ፍቃድ ትምህርት ስለመውሰዳቸው አግባብ ካለው ባለሥልጣን የተሰጠ ሰርተፍኬት፣ አንድ በውጭ አገር የሚገኝ ወኪል በሀገር ውስጥ ከሁለት ኤጀንሲዎች በላይ ውክልና እንደሌለው የሚያሳይ ማስረጃ፣ ሠራተኛን በሚልክበት አገር ወኪሉ የተሟላ ቢሮና ጊዜያዊ የምግብና የመጠለያ አገልግሎት ያለው ስለመሆኑ፣ በኢትዮጵያ ኢምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት (በኢፌድሪ ሚሲዮን ጽ/ቤትና በውጭ ጉዳይ ሚ/ር) የተረጋገጠ ማስረጃ፣ ለቢሮ ሥራ ክትትል ለማድረግ እና የሙያ ምክር አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉ ባለሙያዎች መመደቡን ማስረጃ ሳያሟሉ ፍቃድ መሰጠቱ ተረጋግጧል፡፡

47. በሌላም በኩል በውጭ አገር የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ቅርንጫፍ ቢሮዎቹን ለመክፈት ሚኒስቴር መ/ቤቱን ሲጠይቁ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልል የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ኤጀንሲው በክልሉ ውስጥ ቅርንጫፍ ለመክፈት እንዲችል ትብብር እንዲደረግላቸው የትብብር ደብዳቤ ከመጻፍ ውጪ የትብብር ደብዳቤውን ሲጽፍ በየትኛው ከተማ ወይም ሥፍራ እንደሆነ ሳያረጋግጥ መሆኑ እና በትክክል በየትኛው ስፍራ ቅርንጫፍ ቢሮዎች እንደተከፈቱ ኤጀንሲዎቹም ሆነ ክልሎቹ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የማያሳውቁ ወይም ሪፖርት የማይደረግለት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

48. ፈቃድ ለማግኘት የሚያስችል መስፈርት በአዋጁና በመመሪያው ላይ በግልጽ የተቀመጠው መሟላቱ ሳይረጋገጥ ፈቃድ መስጠቱ እንዲሁም ኤጀንሲዎቹ በየትኛው ከተማ ቅርንጫፍ እንዳላቸው ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲያውቀው አለመደረጉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## ወደ ውጭ ለሥራ የሚሄዱ ሠራተኞች መክፈል የሚገባቸውን የክፍያ ሂሣብ ብቻ የከፈሉ መሆኑን በተመለከተ፣

49. ለሥራ ወደ ውጭ ለመሄድ የሚዘጋጁ ሠራተኞች በአዋጅ ቁጥር 632/2001 መሠረት መክፈል ከሚገባቸው የክፍያ ሂሣብ ሌላ ተጨማሪ ክፍያ እንዲከፍሉ መደረግ የለበትም፡፡

የውጭ ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጄንሲዎችም ሠራተኞቹ መክፈል ያለባቸውን ክፍያ በቢሮዎቻቸው ላይ በሚታይ ቦታ ላይ ሊለጥፉትና የሚልኳቸው ሠራተኞች እንዲያውቁት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

50. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ለተመረጡት 15 ኤጄንሲዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅና በኦዲቱ ወቅት በየኤጄንሲዎቹ ቢሮዎች በአካል በመገኘት በተደረገው ጉብኝት ሁሉም ኤጄንሲዎች ከሠራተኛው የሚጠበቀውን የክፍያ ሂሣብ ዝርዝር ግልጽ በሆነና በሚታይ ቦታ ለጥፈው አለመገኘታቸው ተረጋግጧል፡፡

51. በአዋጅ ቁጥር 632/2001 መሰረት በአሰሪው መሸፈን የሚገባውን የመግቢያ ቪዛ ክፍያን ሠራተኞቹ እንዲከፍሉ እየተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ በኦዲቱ ወቅት መጠይቅ ከቀረበላቸው 72 ወደ ውጭ ለሥራ ለመሄድ ከተዘጋጁ ሠራተኞች እንደተገለጸው በተጨማሪ ያለአግባብ እንዲከፍሉ የተደረገውን የመግቢያ ቪዛ ክፍያን ሳይጨምር ከብር 2,000 (ሁለት ሺህ ብር) እስከ ብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) የሚደርስ በድምሩ ብር 315,808.00 (ሦስት መቶ አስራ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር) ለኤጄንሲዎቹ በብልጫ መክፈላቸውን ገልጸዋል፡፡

52. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ሠራተኞቹ መክፈል የሚገባቸውን ክፍያ በተመለከተ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቅድመ ጉዞ ገለጻ ጊዜ እንደሚነገራቸው፣ ነገር ግን ከዚህ ውጭ ገንዘብ ተጠይቄአለሁ ብለው ወደ ውጭ የሚሄዱ ሠራተኞች አቤቱታ ባለማቅረባቸው የሚያውቁበት መንገድ የሌለና ለቪዛ ተከፈለ የተባለውን ገንዘብ በተመለከተ ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤት ኃላፊዎች እንደገለፁት ሠራተኞቹ ገንዘቡን የሚከፍሉት ለሚሄዱበት አገር ኤምባሲ የቪዛውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በሚል በሰነድ ማረጋገጫ ስም የሚያስከፍሉት ክፍያ በመሆኑ እና ይህ ክፍያ በማን መሸፈን አለበት በሚለው ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየተነጋገሩ መሆናቸውን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ሠራተኞቹ መከፈል ስላለባቸው ክፍያ ሁሉንም ክፍያ አጠናቀው ከፍለው ለጉዞ ከተዘጋጁ በኋላ በሚሰጥ የቅድመ ጉዞ ሥልጠና ላይ ገለጻ ይስጣል የሚለውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

53. መ/ቤቱ በየተወሰነ ጊዜ የዘረጋው ሥርዓት ትክክል በመተግበር ላይ መሆኑን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ማረጋገጥ ሲገባው ያለ አግባብ የሚከፈሉ ክፍያዎች ካሉ የሚያውቅበት ዘዴ የለም ያለውን አልተቀበልነውም፡፡

54. ሠራተኞቹ መክፈል የሚገባቸው እና በአሠሪው መሸፈን የሚገባውን ክፍያ ኤጀንሲዎች በሚታይ ቦታ አለመለጠፋቸውና በአሰሪው መሸፈን የሚገባውን ክፍያ እና ሌሎች ተጨማሪ ክፍያዎችን ሠራተኞቹ እንዲከፍሉ መደረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

**ኤጀንሲዎች ያገኙትን የውጭ ምንዛሪ በአገር ውስጥ ባንክ ገቢ ማድረጋቸውን በተመለከተ፣**

55. የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ከውጭ አገር የሚያገኘውን የውጭ ምንዛሪ በአገር ውስጥ ባንክ ገቢ ለመደረጉ በየ3 ወሩ ለመ/ቤቱ በሪፖርት ማሳወቅ አለበት፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሪፖርት በማያቀርቡት ላይ ክትትል ሊያደርገና እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
56. ነገር ግን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ እንደተቻለው በናሙና ከታዩት 15 የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ውስጥ የውጭ ምንዛሪውን በአገር ውስጥ ባንክ ገቢ ለማድረጋቸው የባንክ ማስረጃ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት ያደረጉበት ማስረጃ አልተገኘም፡፡
57. ለምን በውጭ ምንዛሪ ያገኙትን ገንዘብ በአገር ውስጥ ባንክ ገቢ ለማድረጋቸው ማስረጃ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት እንደማያቀርቡ በናሙና የተመረጡት ኤጄንሲ ኃላፊዎች ተጠይቀው ሪፖርት እንዲያደርጉ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለማያስገድዳቸው የማያቀርቡ መሆኑን ገልጸዋል፡፡
58. የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ኤጀንሲዎች ገቢያቸውን በአገር ውስጥ ባንክ ገቢ ለማድረጋቸው ሪፖርት እንደማያደርጉ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የተወሰኑት ሪፖርት እያደረጉ መሆኑን እና ጅምር ሥራዎች መኖራቸውን ገልጸው ለወደፊት ሁሉም እንዲተገብሩ መመሪያ የተሰጣቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡
59. ለሥራ ወደ ውጭ በሚልኳቸው ሠራተኞች ከቀጣሪው የሚያገኙትን ክፍያ የሚቀበሉት በውጭ ምንዛሪ በመሆኑ፣ ይህንኑ ክፍያ በአገር ውስጥ ባንክ ገቢ እያደረጉ ሪፖርት አለማቅረባቸው አገሪቱ ማግኘት የሚገባትን ተገቢውን የውጭ ምንዛሪ ማግኘቷን ማረጋገጥ የማያስችል በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

**የውጭ ሀገር የሥራ ሥምሪት በጸደቀው የሥራ ውል መሰረት መፈጸሙን ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣**

60. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ውጭ ለሥራ የሄዱ ሠራተኞችን ከሄዱ በኋላ የሚሠሩት ሥራ በትክክል ውሉ ላይ የተመለከተው መሆኑን የሚያረጋግጥበት እና የሚገኙበትን ሁኔታ

ለመከታተል የሚያስችል የመከታተያ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ ሥርዓቱም የሚመለከታቸውን አካላት ሊያሳትፍ ይገባል፡፡

61. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ውጭ ለሥራ የሄዱ ሠራተኞች ከሄዱ በኋላ የሚሠሩት ሥራ በትክክል ውሉ ላይ የተመለከተው መሆኑን የሚያረጋግጥበት እና የሚገኙበትን ሁኔታ ለመከታተል የሚያስችል የክትትል ስርዓት አለመዘርጋቱ ታውቋል፡፡

62. በኦዲቱ ወቅት ከሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ቃለ መጠይቅ ለመረዳት እንደተቻለው፣ ወደ ውጭ የተላኩ ሠራተኞች የሚገኙበትን ወቅታዊ ሁኔታ ለማወቅ የሚደረግ ክትትል የሌለ ሲሆን ክትትልና ቁጥጥር የሚደረገው ከሠራተኛዋ ቤተሰብ ወይም ከራሷ ከሠራተኛዋ አቤቱታ ሲቀርብ ብቻ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

63. ይሁን እንጂ ኩዌት አገር የሚሄዱ ሠራተኞች ከሄዱበት ቀን አንስቶ እስከ 90 ቀን ድረስ ባለው ወኪሉ (ኤጀንቱ) በቦታው በመገኘትም ሆነ በስልክ ክትትል እንደሚያደርግ፣ ይህንንም ክትትል የሚያደርገው ችግር ሲያጋጥም ወይም አቤቱታ ሲቀርብ ብቻ እንደሆነና ከ90 ቀናት በኋላ ግን የሚደረግ ክትትል የሌለ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

64. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በአዋጁ መሰረት መቋቋም የነበረበት ብሔራዊ ኮሚቴ በከፍተኛ አመራር ደረጃ መቋቋሙን፣ በአዋጁ ላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የዜግነትና የኢምግሬሽን ዋና መምሪያ፣ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ፖሊስ፣ የፍትህ አካላት፣ ፍርድ ቤቶች፣ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ትምህርት ሚኒስቴር፣ ተቀናጅተን መስራት እንዳለብን ቢገለጽም በቅንጅት እንድንሠራ ባለመደረጉ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓቱን ለመዘርጋትና ተግባራዊ ለማድረግ ባለመቻሉ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

65. ስለሆነም ዜጎቹ በትክክል በውላቸው ላይ በተገለጸው መሰረት መሥራት ያለባቸውን ሥራ እየሠሩ መሆኑ አለመረጋገጡ ከውል ውጭ እና መብታቸውን በሚነካ ሁኔታ በማስገደድ ከአቅም በላይ በሆነ የሥራ ጫና ላይ እንዳይሰማሩ ለማድረግ እና መብታቸውን ለማስከበር አይችልም፡፡

### በውጭ ሀገር ለሥራ ተሰማርተው የሚመለሱ ዜጎች በአገር ውስጥ በተለያየ የሥራ መስክ እንዲሰማሩ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣

66. በውጭ አገር ለሥራ ተሰማርተው የሚመለሱ ዜጎች በተለያዩ የገቢ ማስገኛ የሥራ መስክ ላይ እንዲሰማሩ ለማደረግ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ይህም ሥርዓት ሲዘረጋም የሚመለከታቸውን የፌዴራልና የክልል ተቋማትን ሊያሳትፍ ይገባል፡፡ በሥራ

ምክንያት ውጭ አገር ቆይተው ለሚመለሱ ዜጎች ስለ አገኙት ገንዘብ አጠቃቀም በተመለከተ ከክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ጋር በመቀናጀት ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

67. በኦዲቱ ወቅት በውጭ አገር ተሰማርተው የሚመለሱ ዜጎችን በተለያዩ የሥራ መስኮች እንዲቋቋሙ ለማገዝ የሚረዳ የፕሮጀክት ፕሮፋይል በሚኒስቴር መ/ቤቱ መዘጋጀቱ የታየ ቢሆንም በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ባለመደረጉ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡ ከውጭ የሥራ ሥምሪት ተመላሽ የሆኑ ዜጎች ያገኙትን ገንዘብና ከቆይታቸው የቀሰሙትን ጠቃሚ ልምዶች በመጠቀም በመረጡባቸዉ አዋጭ በሆኑ የሥራ መስኮች (በመደራጀት ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ማቋቋምን ጨምሮ) እንዲሰማሩ ለማድረግ ከሚመለከታቸው የክልልና የከተማ መስተዳደር ጋራ በመቀናጀት እንዲሠማሩ ለማድርግ የሚያስችል ሥርዓት አለመዘርጋቱም ታውቋል፡፡

68. ሥርዓቱ ለምን ተዘርግቶ ተግባራዊ እንዳልተደረገ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከውጭ ተመላሾችን ለማግኘት የመረጃ እጥረት መኖሩን እና አብዛኛዎቹም ለላኳቸው ኤጀንሲዎች መመለሳቸውን አለማሳወቃቸው እንደ ዋና ችግር መሆኑንና አሁን ግን ዜጎች ወደ አገር ውስጥ እንደተመለሱ የሚረጋግጥበትን መረጃውን ለማግኘት እቅድ እንደያዙና የተዘጋጀውንም የፕሮጀክት ፕሮፋይል ሥራውን ወደ ተግባር ለማሸጋገር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ የሚሠራበትን ሁኔታ እየተነጋገሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

### ለውጭ አገር ሥራ ሥምሪት የተዘጋጀው የሥራ ውል በየዓመቱ መከለሱን በተመለከተ፣

69. ለውጭ አገር ሥራ ሥምሪት የሚዘጋጀው የሥራ ውል በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት በየዓመቱ እየተከለሰ ማሻሻያ ሊደረግበት እና ወቅቱን የጠበቀ ሊሆን ይገባል፡፡

70. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከቀረበው በናሙና የተመረጠ የሠራተኞች ውል እና ቃለ መጠይቅ ለማወቅ እንደተቻለው አሁን እየተሠራበት ያለው የሥራ ውል ከ3 ዓመት በፊት የተዘጋጀ ሲሆን ውሉ በየአመቱ ለመከለሱ መረጃ አልቀረበም፡፡

71. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች የሥራ ውሉ በመመሪያው መሰረት በየአመቱ እየታየ ለምን እንዲከለስ እንዳልተደረገ በመውጫ ስብሰባ ላይ መልስ ሲሰጡ ወደ ውጭ የሚላኩ ሠራተኞች የተሟላ የሙያ ስልጠና ያላገኙ በመሆናቸው ውላቸው እንዲሻሻል ለማድረግ በመጀመሪያ በቂ ሥልጠና ያገኙ ሠራተኞች ብቻ እንዲሄዱ ሲደረግ ውሉ እና የመነሻ ደመወዝ ጭምር ማሻሻያ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

72. የሥራ ውሉ በየአመቱ እየታየ እንዲከለስ አለመደረጉ ተገቢው ሙያና ሥልጠና ያላቸው ዜጎች ሲሄዱ ተገቢውን ክፍያ እና ጥቅማጥቅም ለማስከበር የማያስችል በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## 2.2. በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር በሥራ ተሰማርተው ለሚሠሩ ዜጎች የሥራ ሥምሪት የተደራጀ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ የተዘረጋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ በተመለከተ፣

**በአገሪቱ ያለውን የሥራ ገበያ መረጃ ለመያዝ የተዘረጋውን ስርዓት በተመለከተ፣**

73. በአገሪቱ ውስጥ ያለው የሥራ ገበያ መረጃ በየክልሉ ተሰብስቦ ሊያዝ ይገባል፡፡ የተሰበሰበው መረጃም በአገር ውስጥ ሠራተኞች ሊሸፈኑ የማይችሉ ሥራዎችን በመለየት የሥራ ገበያ መረጃዎችን ከየክልሉ በማሰባሰብ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አጠናቅሮ ሊይዝ ይገባል፡፡ ወጥ የሆነ መረጃ እንዲሰበሰብ ለማድረግ እንዲቻል ሁሉም ክልሎች የሚጠቀሙበት የመረጃ መሰብሰቢያ ፎርማት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተዘጋጅቶ ለክልሎች ሊሰራጭ ይገባል፡ የተያዙትም መረጃዎች ተጠናቅረው እና ተተንትነው ለተጠቃሚው እንዲደርሱ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያደርግ ይገባል፡፡

74. በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው ወጥ የሆነ የሥራ ገበያ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ፎርማት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፍላጎቱን የሚያሟላ ተዘጋጅቶ ለመሰራጨቱ መረጃ አልቀረበም፡፡ በኦሮሚያ ሠራተኛና ማኅበራዊ ኤጀንሲ አጠቃላይ የሥራ መረጃዎቹ የሚሰበሰቡ ሲሆን የሚላክላቸው መረጃ ግን የተሟላ አለመሆኑን፣ ስለዚህ ከተሰበሰበው መረጃ የተሟላ የሆነውን ብቻ ለሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በየአመቱ እንደሚያሳውቁ ገልጸዋል፡፡ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ በበኩሉ ያለውን የሥራ ገበያ መረጃ እንደሚሰበስብ እና በየአመቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት እንደሚያደርጉ ለተላከላቸው መጠይቅ በሰጡት መልስ ላይ ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን የሚቀርቡት የሥራ ገበያ መረጃዎች በአገር ውስጥ ዜጋ ሊሸፈኑ የሚችሉ እና የማይችሉትን ለይቶ የማያሳይ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ክልሎች ግን ለተላከላቸው መጠይቅ መልስ፣ አልሰጡም፡፡

75. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ አሁን ያለው የመረጃ ስርዓት ክፍተት ያለውና የተሟላ ስላልሆነ ያለውን ክፍተት ለማወቅ በአጠቃላይ በውጭ አገር ዜጎች የሚከናወኑ ሥራዎች በአገር አቀፍ ደረጃ በአማካሪ ድርጅቶች ተጠንተው ያለው የመረጃ ሥርዓት እንዲሻሻል ለማድረግ አማካሪ ተቀጥሮ ሥራው ሰኔ 30/2003 የተጀመረ

መሆኑንና ነገር ግን ጥቅል የሥራ ገበያ መረጃዎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያወጣው ሌበር ቡሌቲን/መጽሔት በየዓመቱ እንደሚወጣ አስታውቀዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከኃላፊዎቹ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እየተዘጋጀ ይወጣል የተባለው የሥራ ገበያ መረጃ የያዘ መጽሔትም የሚዘጋጀው በእንግሊዘኛ ቋንቋ መሆኑ እንጂ በአማርኛ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

76. በመቀጠልም ከክልሎች የሚሰበሰበውን የሥራ ገበያ መረጃን አስመልክቶ የሥራ ሥምሪት የመረጃ ሥርዓትን ሊያስተላልፍ የሚችል EESI የሚባል ሶፍት ዌር ተዘጋጅቶና ለክልል ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቶ እንደነበርና፣ ነገር ግን በየክልሉ በሶፍት ዌር ላይ የሰለጠኑ ባለሙያዎች በመልቀቃቸውና በቂ የሰው ኃይል ባለመኖሩ ትግበራው ሊቋረጥ መቻሉን በቀጣይም ከክልሎች ጋር በኔትወርክ እና በመረጃ መረብ መረጃ ለመለዋወጥ መታቀዱን ገልጸዋል፡፡

77. ወጥ የሆነ የሥራ ገበያ አለመሰብሰቡ በአገር ውስጥ ያለውን የሥራ ፍላጎት ለማወቅ እንዲሁም በተሟላ መረጃ ላይ የተመሰረተ የፖሊሲ ውሳኔ ለመስጠት አዳጋች ያደርገዋል፡፡

**የሥራ ፈቃድ የተሰጣቸው የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ሥምሪት ከሚያደርጉበት ክልል ጋር ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘረጋው የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓትን በተመለከተ፣**

78. በኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ለመሰማራት የሥራ ፈቃድ የተሰጠው የውጭ አገር ዜጋ የሚሠራበት ድርጅት ላለበት ክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የውጭ ዜጋውን በተመለከተ መረጃው ሊተላለፍ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ከክልሎች ጋር በመቀናጀት የውጭ ሀገር ዜጎች ፈቃድ በተሰጣቸው የሥራ መስክ ላይ መሰማራታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

79. በኦዲቱ ወቅት ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ ቢሮ ከቀረበው ቃለ መጠይቅ ለመረዳት እንደተቻለው ለክልሉ ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ እስከ ጥቅምት 2004 ድረስ ከሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ፍቃድ ስለተሰጣቸው እና በክልሉ ስለተሰማሩ የውጭ ሀገር ዜጎች የሚደርሳቸው መረጃ እንዳልነበረ ገልጸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለውጭ ሀገር ዜጎች የሥራ ፍቃድ ሲሰጥም ሆነ ሲታደስ ለክልሉ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ እንደማያሳውቅ ገልጸዋል፡፡

80. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተላከለት መረጃ ከ1999 እስከ 2000 ዓ.ም ባለው

ጊዜ ውስጥ የ11 የውጭ አገር ዜጎች በመስከረም 2004 ደግሞ የ1 የውጭ አገር ዜጋ በድምሩ የ12 የውጭ አገር ዜጎች መረጃ ብቻ እንደደረሰው፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ደግሞ መረጃው እንዳልደረሰው እና ክትትልም እንደማያደርግ ለተላከላቸው መጠይቅ በሰጡት መልስ ላይ አስታውቀዋል፡፡

81. ባለፉት ሦስት በጀት ዓመታት(ከ2001-2003) ለ14,773 የውጭ አገር ዜጎች በተለያዩ ክልሎች ውስጥ ለሥራ ለሚሰማሩ የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ የተሰጠ ቢሆንም የሠራተኞቹ መረጃ ለየክልሎቹ እንዳልተላለፈ ታውቋል፡፡ አብዛኛው የሥራ ፈቃድ የተሰጠው አዲስ አበባ (12,015) ሲሆን በመቀጠልም ኦሮሚያ (1,903)፣ ትግራይ (414)፣ ድሬዳዋ (302)፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል (83) ውጭ አገር ዜጎች ፈቃድ እንደተሰጣቸው ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ከቀረበልን መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በየክልሉ የሥራ ፈቃድ ተሰጥቷቸው የተሰማሩት የውጭ ዜጎች ስርጭት ዝርዝር በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

<u>ከ2001 እስከ 2003 ዓም በሀገር ዉስጥ በተለያዩ ክልሎች በስራ የተሰማሩ</u>

<u>የዉጭ ሀገር ዜጋ ሠራተኞች ብዛት</u>

| ተራ ቁጥር | ክልል | የሥራ ፈቃድ የተሰጣቸው የውጭ ዜጎች ብዛት |
|---|---|---|
| 1. | አዲስ አበባ | 12015 |
| 2. | አፋር | 7 |
| 3. | አማራ | 34 |
| 4. | ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ | 4 |
| 5. | ድሬዳዋ | 302 |
| 6. | ጋምቤላ | 3 |
| 7. | ኦሮሚያ | 1903 |
| 8. | ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች | 83 |
| 9. | ሶማሌ | 8 |
| 10. | ትግራይ | 414 |
| | ጠቅላላ ድምር | 14,773 |

82. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ከሰኔ 2003 ዓ.ም. ጀምሮ ፈቃድ ያገኙ የውጭ አገር ዜጎች ዝርዝር፣ የሥራ ፈቃድ ቁጥርና የሥራ ፈቃዱ የሚያገለግልበትን ጊዜና የውጭ አገር ዜጎች ፓስፖርት ቁጥር የያዙ መረጃዎች ለየክልሉ አስፈላጊውን ክትትል እንዲያደርጉ የላኩና፣ በየክልሉ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪዎች ስላሉ ቁጥጥሩ የሚደረገው በነርሱ በኩል መሆኑንና፣ ነገር ግን ከሰኔ 2003 ዓ.ም.በፊት የሥራ ፈቃድ የተሰጣቸው የውጭ አገር ዜጎች መረጃ ግን ለምን እንዳልተላለፈ መልስ አልሰጡም፡፡

83. የሥራ ፈቃድ የተሰጣቸው የውጭ አገር ዜጎች መረጃ ለክልሎች አለመተላለፉ ክልሎች ለሚያደርጉት የክትትልና የቁጥጥር ሥራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሮአል፡፡

## 2.3 ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተቀጥረው ስለሚሰሩ የውጭ አገር ዜጎች የፈቃድ አሰጣጥ ና የሥራ ስምሪት ቀልጣፋና ፍትሀዊ መሆኑን በተመለከተ፣

**ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ፣**
**የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓትን በተመለከተ፣**

84. ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የሥራ ፈቃድ የወሰዱ የውጭ ዜጎችም ፈቃድ በወሰዱበት የሥራ መስክ ላይ መሰማራታቸውን ለማረጋገጥ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

85. ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ የቁጥጥር ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት በሱፐር ሻይን ኤንቨስትመንት እና በሱፐር ማክስ ኦፕቲካል ሜዲካል ፒ.ኤል.ሲ. ውስጥ ተቀጥረው ስለሚሰሩ 19 የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲላቸው ጠይቆ የቀረበለት መረጃን በመጠራጠሩ ይህንን ለማጣራት ጉዳዩን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በደብዳቤ ቁጥር 6.6/2/3/3/85 በመስከረም 04 2002 ዓ.ም. ቀን ቢጠይቅም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀ ድረስ ለቢሮው መልስ አለመሰጠቱ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚገኘው የድርጅቱ ማኅደር ውስጥም ለእነዚህ 19 ሠራተኞች የሥራ ፈቃድ የተሰጠበት መረጃ ተያይዞ አልተገኘም፡፡

86. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ፈቃድ የተሰጣቸው የውጭ አገር ዜጎች መረጃዎች በተሟላና በዘመናዊ መልኩ በመረጃ ቋት ውስጥ ማስገባት የተጀመረው ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑና ቁጥራቸው የተገለጸው የውጭ ሀገር ዜጎች መረጃዎች በአዲስ መልክ ተደራጅቶ ወደ ኮምፒዩተር በገባው የመረጃ ቋት ውስጥ

ተፈልገው ሊገኙ ባለመቻላቸው አሁንም እነዚህ ተፈላጊ መረጃዎችን ጊዜ በመውሰድ በመ/ቤቱ መዝገብ ቤት ባሉ ማኅደሮች ውስጥ በማፈላለግ ለማግኘት ጥረት እየተደረገ ይገኛል ብለዋል፡፡

87. ፈቃዱ ከተሰጠ በኋላም ስለ አፈጻጸሙ  በሚ/ር መ/ቤቱ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የውጭ አገር ዜጎች በተሰጣቸው የሥራ ፈቃድና ፈቃዱን በጠየቀላቸው ድርጅት ውስጥ እየሠሩ ስለመሆኑ በየክልሉ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪዎች ስላሉ ክልሎች እንዲከታተሉ ከሰኔ 2003 ጀምሮ ፈቃድ ያገኙ የውጭ አገር ዜጎች ዝርዝር የሥራ ፈቃድ ቁጥርና የሥራ ፈቃዱ የሚያገለግልበትን ጊዜና የውጭ አገር ዜጎች ፓስፖርት ቁጥር የያዙ መረጃዎች ማስተላለፋቸውን ገልጸዋል ፡፡

**ለውጭ ዜጎች የሥራ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ሥራው በኢትዮጵያውያን አለመሸፈኑ መረጋገጡን በተመለከተ፣**

88. ለውጭ ዜጎች የሥራ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ሥራው በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ሊሸፈን አለመቻሉ ወይንም በመስኩ የባለሙያ እጥረት መኖሩ በቅድሚያ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ አሰሪዎችም ፈቃድ ሲጠይቁ ባለሙያው በአገር ውስጥ ሊገኝ አለመቻሉን የሚያሳይ ማስረጃ ከሥራ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻው ጋር አብረው ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

89. ይሁን እንጂ  ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ሲጠየቅ ሥራው በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ሊሸፈን አለመቻሉ፣ በተጠየቀው መስክ ኢትዮጵያዊ ባለሙያ የሌለ ወይም እጥረት መኖሩ፣ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት በቅድሚያ ፈቃድ የሚጠይቁት ድርጅቶች /አሠሪዎች እንዲያረጋግጡ አይደረግም፡፡ ለውጭ አገር ዜጎች  የሥራ  ፈቃድ  ለመስጠት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ የሚወሰንበት መመሪያ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀ ቢሆንም፣ የተዘጋጀው መመሪያ በየትኛው የሥራ መስክ የውጭ ዜጎች መሠማራት እንዳለባቸው እና እንደሌለባቸው የሚገልጽ መስፈርት አላስቀመጠም፡፡

90. ስለጉዳዩ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን የኢንዱስትሪ ግንኙነት እና ማኅበራት ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ ተጠይቀው ሲመልሱ፣ በአገር ውስጥ ባለሙያ የሚሸፈን ሥራ በውጭ ዜጎች እንዲሸፈን መደረጉ የሥራ አጥ ቁጥርን ከመጨመሩም በላይ በሙያው

ብቃት ያላቸው ዜጎች ያላቸው የሥራ ተነሳሽነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር በመሆኑ ጉዳዩ ጠንክሮ ሊሠራበት የሚገባ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

91. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ከተሰጣቸው የሥራ መስኮች መካከል 132 ሰራተኞች በሂሳብ አያያዝ (accountant)፣ 223 በአናጢነት (Carpenter)፣12 በጸሀፊ (Secretaries)፣ 30 በስፌትና ተመሳሳይ ስራዎች ('TEXTILE, GARMENT AND RELATED TRADES WORKERS)፣ 43 ፋይናንስ ማናጀር፣ 63 ምግብ አብሳይ፣ 15 ሾፌር፣ 13 ገንዘብ ያዥ፣ 254 አሰተማሪዎች፣ 20 ቀለም ቀቢ፣ 11 እንጨት ሠራተኛ ይገኙበታል፡፡

92. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ አዋጁን መሠረት በማድረግ በጥር 2002 መሰረት የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበት መመሪያ ወጥቶ እየተሰራ እንደሚገኝና በዜጎች ሊሸፈኑ የሚችሉ የሥራ መስኮችን በመለየት ለውጭ ዜጎች ፈቃድ ለመስጠትም ሆነ ለመከልከል የሚለይበት መስፈርት ያልተዘጋጀበት ምክንያት ያለው የሥራ ገበያ መረጃ የተሟላ ባለመሆኑ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

93. የውጭ አገር ዜጎች ሊሠማሩበት የሚገባው የሥራ መስክ ተለይቶ አለመታወቁ በአገር ውስጥ ባለሙያ ሊሸፈን በሚችል የሥራ መስክ ሁሉ የሥራ ፈቃድ እንዲሰጥ በር የሚከፍት በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

### ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ሲሰጥ ለተባለው የሥራ መስክ ተገቢው ሙያ ያላቸው መሆኑን መረጋገጡን በተመለከተ፣

94. ለውጭ ዜጎች የሥራ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት በተጠየቀው የሥራ መስክ ተገቢው የትምህርት ማስረጃ እና የሥራ ልምድ እንዳላቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ይህንን ማስረጃ አሟልተው ለማያቀርቡ የሥራ ፈቃድ ጥያቄ አመልካቾች የሥራ ፈቃድ ሊሰጥ አይገባም፡፡

95. ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ለመስጠት መመሪያ ተዘጋጅቶ ፈቃዱ የሚሰጥበት መስፈርት ወጥቷል፡፡ ነገር ግን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት የሥራ ፈቃድ ከተሰጣቸው 23 የውጭ ዜጎች ፋይል ውስጥ ለመረዳት እንደተቻለው በተመለከትናቸው ከ23 የሥራ ፈቃድ ከተሰጣቸው የውጭ አገር ዜጎች ውስጥ የ10 ሠራተኞች የትምህርት ማስረጃ በሠራተኛው ማህደር ውስጥ ተያይዞ አለመገኘቱ ተረጋግጧል፡፡ የሥራ ፈቃድ በተጠየቀበት የሥራ መስክ የሚያስፈልገው የ10 ሠራተኞች የትምህርት ማስረጃም ሆነ የሥራ ልምድ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

96. ሚኒስቴር መ/ቤቱን በመወከል የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለወሰዱ የውጭ አገር ዜጎች ፈቃድ ሲሰጥ ለተጠየቀው የሥራ መስክ አስፈላጊው

የትምህርት ማስረጃና የሥራ ልምድ መኖሩን ሳያረጋግጥ ፈቃድ እንደሚሰጥ፣ እንዲሁም በየአመቱ ለፈቃድ እድሳት ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲመጡ የጎደለውን የትምርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ እንዲያሟሉ የማይደረግ መሆኑ ታውቋል፡፡

97. ለምን ተገቢው የትምህርት እና የሥራ ልምድ ማስረጃ እንደማይያያዝ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የኢንቨስትመንት ኤጄንሲ ፈቃድ ሲሰጥ በዋነኛነት የሚያየው የኢንቨስተሩን ካፒታል በመሆኑ የሥራ ፈቃድ ሲሰጥ ለትምህርት ማስረጃ ትኩረት እንደማይሰጥ፣ ለእድሳትም ሲመጡም ወደኋላ ሄደው የትምርት ማስረጃም ሆነ የሥራ ልምድ እንዲያመጡ እንደማያደርጉ፣ የመንግሥት ድርጅት ያስመጣው ከሆነ ድርጅቱ ደብዳቤ ከጻፈ ለሠራተኞቹ የሥራ ፈቃድ እንደሚሰጡ፣ ለግል ድርጅቶች ለመሣሪያ ተከላና የመሣሪያ ብቃት ለማረጋገጥ ለሚመጡም የትምህርት ደረጃቸው እና ልምዳቸው ሳይረጋገጥ እንዲሁ የሥራ ፈቃድ ይሰጣል ብለዋል፡፡ ከዚህ ውጭ ከጥር 2002 በፊት የነበረው መመሪያ የትምህርት ማስረጃ እንዲያቀርቡ ስለማያስገድድ ሳይጠየቁ ፈቃድ ይሰጥ እንደነበረ አሁን ግን ተገቢው የሥራ ልምድና የትምህርት ማስረጃ እየቀረበ ፈቃድ እንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ በሠራተኞቹ ፋይል ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

98. የሥራ ፈቃዱ በሚሰጥበት ጊዜ የውጭ አገር ሠራተኛው የሥራ ፈቃዱን ለጠየቀበት የሥራ መስክ ተገቢው የትምህርት ማስረጃ እና ልምድ ያለው መሆኑ ሳይረጋገጥ ፈቃድ መስጠቱ ለህገ-ወጥ አሰራር በር ይከፍታል፡፡

### ተቀጥረው የሚመጡ የውጭ ዜጋ ሠራተኞች በሚሰሩበት ቦታ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን የቴክኒክ ወይም የክህሎት ሽግግር የሚያደርጉበት ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣

99. በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያየ የሥራ መስክ ተቀጥረው የሚመጡና የሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/1994 አንቀጽ 16/2 መሠረት ክህሎታቸውን ለኢትዮጵያውያን ሠራተኞች በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ማስተላለፍ አለባቸው፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይህ ተግባራዊ ለመደረጉ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ፈቃድ ከመታደሱ በፊት የቴክኒክ ክህሎት ሽግግር መደረጉን ወይም ሊደረግ ያልቻለበትን ሁኔታ በቅደሚያ ሊያጣራ ይገባል፡፡

100. በዚሁ መሰረት በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የውጭ አገር ዜጎች ተቀጥረው በሚሠሩበት ድርጅት በእነሱ የሚተኩ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች እንዲሠለጥኑ ማድረግ

እንደሚገባቸው እና ይህንንም በሪፖርት መልክ እንዲያሳውቁት፣ ተተኪ ኢትዮጵያውያን ማፍራት ካልቻሉ አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ እንዳለባቸው በመመሪያ መልክ ማውጣቱ ታይቷል፡፡

101. ይሁን እንጂ የውጭ ሀገር ዜጎቹ በተቀጠሩበት ድርጅት ውስጥ ተተኪ ኢትዮጵያውያን እንዲሰለጥኑና የክህሎት ሽግግር እያደረጉ መሆኑን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት እያቀረቡ ስለመሆኑ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ የሥራ ፈቃድ ሲታደስም ተተኪ ባለሙያ ሊያፈራ ያልቻለበት ምክንያት ሳይቀርብ ፈቃዱ እንደሚታደስ ታውቋል፡፡ እንደዚሁም ኢትዮጵያውያን ሠራተኞችን ለማብቃት የእውቀትና የክህሎት ሽግግር እየተከናወነ መሆኑን ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓትም ተዘርግቶ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡

102. የዕውቀትና የክህሎት ሽግግር እየተከናወነ ስለመሆኑ ለማጣራት፤ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን የኢንዱስትሪ ግንኙነት እና ማኅበራት ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ እስከአሁን በአላቸው መረጃ መሰረት አንድ ድርጅት ብቻ የቴክኒክ ክህሎት ለኢትዮጵያውያን ሠራተኞች እያካፈለ መሆኑን፣ በሌሎቹ ድርጅቶች ግን የቴክኒክ ክህሎት ሽግግር እየተደረገ ነው ለማለት እንደማያስችል ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ሠራተኛው አግባብ ያለው የቴክኒክ ክህሎት ሽግግር እንዲያገኝ ለማድረግ የተጠናከረ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

103. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የቴክኒክ ክህሎት ሽግግር ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘረጋ እና መመሪያም የወጣ ቢሆንም በባለሙያ እጥረት ምክንያት ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

104. ስለሆነም በተለያየ ሙያ የተሰማሩ የውጭ አገር ዜጎች በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የክህሎት ሽግግር እያደረጉ ለመሆኑ የክትትል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ አገሪቷ በቂ የሰለጠነ ባለሙያ ለማፍራት ለምታደርገው ጥረት አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚፈጥር ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

# ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሀሳቦች

105. በውጭ ሀገር ስለሚሰሩ ኢትዮጵያውያን ሰራተኞች የስራ ስምሪት ደህንነት አጠባበቅ ቀልጣፋና ፍትሐዊ መሆኑን ማረጋገጥን በተመለከተ፣

- ወደ ውጭ አገር ለሥራ የሚሠማሩ ሠራተኞች የሥራ ውል በቀጣሪው ያልተፈረመ እና በኢትዮጵያ ኤምባሲ /ቆንስላ ያልተረጋገጠ ውል በሚኒስቴር መ/ቤቱ መጽደቁ፣
- ወደ ውጭ አገር ሠራተኛ የሚልኩ ኤጀንሲዎች የላኳቸውን ሠራተኞች ለሥራ በሄዱበት አገር የሥራ ፈቃድ ማግኘታቸውን በማረጋገጥ በወኪሎቻቸው አማካኝነት በአቅራቢያው ወደሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይንም ቆንስላ ጽ/ቤት አቅርበው የማያስመዝገቡ መሆናቸው፣
- ለሥራ ወደ ውጭ አገር የሄዱ ዜጎች የሥራ ውላቸው ሲታደስ እና ሲሻሻል በአቅራቢያው ወደሚገኝ የኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት ቀርቦ እንዲጸድቅና ለሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲያውቀው ሪፖርት አለመደረጉ፣
- የሚኒስቴር መ/ቤቱ በክትትልና በቁጥጥር ወቅት በሚታዩ ጉድለቶች ላይ ማስተካከያ ያላደረጉ ኤጀንሲዎች ላይ ፈቃዳቸው ያልታገደ ብሎም ያልተሰረዘ መሆኑ፣
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለቀረቡ አቤቱታዎች መፍትሔ ስለማግኘታቸው መረጃው ተጠናቅሮ የማይያዝ መሆኑ፣
- የውጭ ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች የሚልኳቸው ሠራተኞች ተገቢው የሙያ ክህሎት ወይንም ሥልጠና ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የማያቀርቡ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም የማይጠይቅ መሆኑን፣
- የውጭ ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ፈቃድ ከማግኘት በፊት ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርት ሳያሟሉ ፈቃድ የሚሰጣቸው መሆኑ፣
- የውጭ ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ቅርንጫፍ ቢሮዎች በተለያዩ ከተሞች ሲከፍቱ ቅርንጫፍ ቢሮዎቹ ያሉበትን አድራሻ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የማያሳውቁ መሆኑን፣
- የውጭ ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ከሠራተኛው የሚጠበቀውን የክፍያ ዝርዝርን ግልጽ በሆነ በሚታይ ቦታ የማይለጥፉ መሆኑን፣

- የውጭ ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች በአዋጁ መሠረት በአሰሪው መሸፈን የሚገባውን የመግቢያ ቪዛ ክፍያን ጨምሮ በሠራተኛው መሸፈን ከሚገባው ክፍያ ውጭ እያስከፈሉ መሆኑን፣
- የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ከውጭ አገር የሚያገኙትን የውጭ ምንዛሪ በአገር ውስጥ ባንክ ገቢ ስለመደረጉ በየ3 ወሩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በሪፖርት የማያሳውቁ መሆኑን፣
- ወደ ውጭ የተላኩ ሠራተኞች የሚገኙበትን ወቅታዊ ሁኔታ ለማወቅ የሚደረግ የክትትል ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በውጭ ሀገር ለሥራ ተሰማርተው የሚመለሱ ዜጎች በአገር ውስጥ በተለያየ የሥራ መስክ እንዲሰማሩ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- ለውጭ አገር ሥራ ሥምሪት የተዘጋጀው የሥራ ውል በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት በየዓመቱ የማይከለስና ወቅታዊ የማይደረግ መሆኑ፣

106. በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር በሥራ ተሰማርተው ለሚሠሩ ዜጎች የሥራ ስምሪት የተደራጀ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥን በተመለከተ፣

- ወጥ የሆነ የሥራ ገበያ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ቅጽ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተዘጋጅቶ ለክልሎችና ለከተማ መስተዳደሮች ያልተሰራጨ መሆኑ፣
- ለውጭ ሀገር ዜጎች የስራ ፍቃድ ሲሰጥም ሆነ ሲታደስ ለየክልሉ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች እንዲያውቁት የማይደረግ መሆኑ፣

107. ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተቀጥረው ስለሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች የፈቃድ አሰጣጥና የሥራ ስምሪት ቀልጣፋና ፍትሀዊ መሆኑን ማረጋገጥን በተመለከተ፣

- የሥራ ፈቃድ የሚጠይቁ የውጭ ዜጎች የሥራ ፈቃድ በሚጠይቁበት ወቅት ለሚጠይቁት የሥራ መስክ የሚያስፈልገው የትምህርት ማስረጃም ሆነ የሥራ ልምድ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የማይገደዱ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ፈቃድ ከመታደሱ በፊት በውጭ ዜጋ በተያዘው የሥራ መስክ ለኢትዮጵያውያን የቴክኒክ ክህሎት ሽግግር መደረጉንና አለመደረጉን ሳያረጋግጥ ለውጭ ዜጎች የሥራ ፈቃድ የሚያድስ መሆኑ፣

- ለውጭ አገር ዜጎች  የሥራ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ሥራው በኢትዮጵያውያን አለመሸፈኑ እንዲረጋገጥ አለመደረጉ

በአጠቃላይ  ዜጎች በውጭ አገር የሚያደርጉትን የሥራ ስምሪት እና የውጭ አገር ዜጎች በኢትዮጵያ ውስጥ የሥራ ስምሪትን አስመልክቶ የሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን ለመወጣት እና ከዚህ ተግባር ጋር በተያያዘ የሚሳተፉ አካላትን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እንቅስቃሴ እያደረገ ቢሆንም በዉጭ ሀገር ስለሚሠሩ ኢትዮጵያዉያን ሠራተኞች የሥራ ስምሪት ደኅንነት አጠባበቅ፣ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር በሥራ ተሰማርተው ለሚሠሩ ዜጎች የሥራ ስምሪት የተደራጀ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝን እና ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተቀጥረው ስለሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች የፈቃድ አሰጣጥና የሥራ ስምሪትን አስመልክቶ  የታዩት ግድፈቶች ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን በተገቢው ሁኔታ እንዲወጣ ስለማያደረገውና ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚሰጠው አገልግሎት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠቃሚዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች ሊያሻሽሉ ይችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች

108. በውጭ ሀገር ስለሚሠሩ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች የሥራ ስምሪት ደህንነት አጠባበቅ ቀልጣፋና ፍትሐዊ መሆኑን ማረጋገጥ ሥር የተገኙ ግኝቶችን በተመለከተ

- ወደ ውጭ አገር ለሥራ የሚሠማሩ ሠራተኞች የሥራ ውል በቀጣሪው ሲፈረምና አሰሪው በሚገኝበት የኢትዮጵያ ኤንባሲ /ቆንስላ / ጽ/ቤት ሲረጋገጥ ብቻ ውሎቹ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊጸድቁ ይገባል፡፡
- ወደ ውጭ አገር ሠራተኛ የሚልኩ ኤጀንሲዎች የላኳቸውን ሠራተኞች ለሥራ በሄዱበት አገር የሥራ ፈቃድ ማግኘታቸውን በማረጋገጥ በ15 ቀናት ውስጥ፣ የሥራ ውላቸው ሲታደስ እና ሲሻሻልም እንዲሁ በወኪሎቻቸው አማካኝነት በአቅራቢያው ወደሚገኘው የኢትዮጵያ ኤንባሲ ወይንም ቆንስላ ጽ/ቤት አቅርበው ሊያስመዘግቡ ይገባል፡፡ የተሻሻለው ውልም ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንዲያውቀው ሪፖርት ሊደረግለት የሚገባ ሲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይህ መደረጉን ለመከታተል የሚያስችለው ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ሠራተኞቹ የሚፈርሙት ውልም በየአመቱ እየተከለሰ ወቅታዊ የሚደረግበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክትትልና በቁጥጥር ወቅት በሚታዩ ጉድለቶች ላይ ማስተካካያ እንዲያደርጉ የጊዜ ገደብ በማስቀመጥና ማስተካከያ መውሰዳቸውን በየጊዜው ክትትል እያደረገ የማያሻሻያ እርምጃ በማይወስዱ የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎችን በአዋጁ መሰረት የሰጣቸውን ፈቃድ ሊያግድ ብሎም ሊሠርዝ ይገባል፡፡
- በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ ለሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ለሚቀርቡ አቤቱታዎች መፍትሔ በሚመለከተው አካል እንዲሰጠው ሊደርግና የተሰጡት መፍትሔዎችን በተመለከተ በጽሑፍ መረጃው ተጠናቅሮ የሚያዝበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የውጭ ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች የሚልኳቸው ሠራተኞች ተገቢው የሙያ ክህሎት ወይንም ሥልጠና ያላቸው እንዲሆኑ ሥልጠና የሚሠጡበት እና ማስረጃውን የሚያቀርቡበት፣ ወይንም የተባለው ክህሎት ያላቸው ከሆነ መረጃውን ለሚኒስቴር

መ/ቤቱ የሚያቀርቡበት እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም የቀረበው መረጃ ትክክለኛ መሆኑን በማረጋገጥ የሥራ ውል እንዲጸድቅ የሚያደርግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለውጭ ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት በአዋጁና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባወጣው መመሪያ ላይ የተቀመጠውን መስፈርት ሙሉ ለሙሉ ሳያሟሉ ፈቃድ መስጠት የሌለበት እና ፈቃድ ከወሰዱ በኋላም ለፈቃድ እድሳት ሲመጡም የተጠቀሱት መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑን በማረጋገጥ ፈቃድ የሚያድስበት የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ኤጀንሲዎችም ፈቃድ ከወሰዱ በኋላ በፈቃዱ ላይ ከተጠቀሰው አድራሻ በተጨማሪ በሌላ ሥፍራ/ከተማ ቅርንጫፍ ቢሮዎች ሲከፍቱ ቅርንጫፍ ቢሮዎቹ ያሉበትን አድራሻ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲያሳውቁት የሚያደርግበት አሠራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የውጭ ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ከሠራተኛው የሚጠበቀውን የክፍያ ዝርዝርን ግልጽ በሆነ በሚታይ ቦታ ሊለጥፉ ይገባል፡፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱም አገናኝ ኤጀንሲዎች ይህን ማድረጋቸውን ሊቆጣጠር እና ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች በአዋጁ መሠረት የመግቢያ ቪዛ ክፍያን ጨምሮ በአሰሪው መሸፈን የሚገባውን ክፍያ ሠራተኞቹ እንዲሸፍኑ አለመደረጉን የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ከውጭ አገር የሚያገኙትን የውጭ ምንዛሪ በአገር ውስጥ ባንክ ገቢ ማድረጋቸውን በየ3 ወሩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በሪፖርት እንዲያሳውቁት የሚያደርግበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ወደ ውጭ የተላኩ ሠራተኞች የሚገኙበትን ወቅታዊ ሁኔታ ለማወቅ የሚመለከታቸውን አካላት ያሳተፈ የክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከሚመለከታቸው የፌዴራል እና የክልል አካላት ጋር በመቀናጀት በውጭ ሀገር ለሥራ ተሰማርተው የሚመለሱ ዜጎች በአገር ውስጥ በተለያየ የሥራ መስክ እንዲሰማሩ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡፤

109. በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር በሥራ ተሰማርተው ለሚሠሩ ዜጎች የሥራ ስምሪት የተደራጀ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ የተገኙ ግኝቶችን በተመለከተ፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአገሪቱ ያለውን የሥራ ገበያ መረጃ ለመሰብሰብና በየጊዜው ወቅታዊ ለማድረግ የሚያስችል ወጥ የሆነ ፎርማት አዘጋጅቶ ለክልሎች እና ለከተማ መስተዳድሮች ሊያሰራጭ፣ ስለአጠቃቀሙ ሥልጠና በመስጠት የተሟላ የሥራ ገበያ መረጃ የሚሰበሰብበትንና ለተጠቃሚዎች የሚሠራጭበትን አሠራር በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለውጭ ሀገር ዜጎች የሥራ ፍቃድ ሲሰጥም ሆነ ሲታደስ ሠራተኞቹ ለሚሠሩበት ክልል የሠራተኛና ማኀበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች እንዲያውቁት ሊያደርግና ከእነርሱ ጋር በመቀናጀት በፈቃዳቸው መሠረት እየሠሩ መሆኑን ለመከታተል የሚያስችለውን አሠራር መዘርጋት አለበት፡፡

110. ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተቀጥረው ስለሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች የፈቃድ አሰጣጥና የሥራ ስምሪት ቀልጣፋና ፍትሀዊ መሆኑን ማረጋገጥን ሥር የተገኙ ግኝቶችን በተመለከተ፣

- የሥራ ፈቃድ የሚጠይቁ የውጭ ዜጎች የሥራ ፈቃድ በሚጠይቁበት ወቅት ለሚጠይቁት የሥራ መስክ የሚያስፈልገው የትምህርት ማስረጃም ሆነ የሥራ ልምድ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሊደረግ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለውጭ ዜጋ የሥራ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ሥራው በኢትዮጵያውያን ሊሸፈን አለመቻሉ በቅድሚያ ሊጣራ የሚገባና የውጭ ዜጋዎች ሊሰማሩበት የተገባ የሥራ መስክ እና መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የሥራ ፈቃድ ከመታደሱ በፊት በውጭ ዜጋ በተያዘው የሥራ መስክ ለኢትዮጵያውያን የቴክኒክ ክህሎት ሽግግር መደረጉንና አለመደረጉን እንደዚሁም ለምን ተተኪ ባለሙያ ሊፈራ እንዳልቻለ ሳይረጋገጥ ለውጭ ዜጎች የሥራ ፈቃድ መታደስ የለበትም፡፡

በአጠቃላይ በውጭ አገር ስለሚሠሩ ኢትዮጵያውያን የሥራ ሥምሪትና ደህንነትን ለመጠበቅ እንዲሁም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተቀጥረው ስለሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር የመስጠት ዓላማውን ለማሳካት በውጭ ሀገር ተቀጥረው ስለሚሰሩ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች የሥራ ስምሪት ደኅንነት አጠባበቅ ቀልጣፋና

ፍትሀዊ መሆኑን ማረጋገጥ፣ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር በሥራ ተሰማርተው ለሚሠሩ ዜጎች የሥራ ስምሪት የተደራጀ ዘመናዊና ወቅታዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት መዘርጋቱን ማረጋገጥ እና ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተቀጥረው ስለሚሰሩ የውጭ አገር ዜጎች የፈቃድ አሰጣጥና የሥራ ስምሪት ቀልጣፋና ፍትሀዊ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚኒስቴር መ/ቤቱን፣ ከሥራ ሥምሪት ጋር በቀጥታና በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው እና የሚሠሩ የፌዴራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም የግል ባለሀብቶችን ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ ይህንንም ለማሳካት በፌዴራል እና በክልል የሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት ተቆጣጣሪ አካላት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖራቸው ይታመናል፡፡ በዚህ ሪፖርት የተገለጹት ግኝቶች፣ መደምደሚያዎች እና የማሻሻያ ሀሳቦች በቀጥታ የሚኒስቴር መ/ቤቱን የማይመለከቱ ቢኖሩ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ስለሚያግዘው በተጠቀሱት ችግሮች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በማሳወቅ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡

በመጨረሻም በሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው የፌዴራል እና የክልል መ/ቤቶች፣ የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

**አባሪ 1**

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| 1. በውጭ ሀገር ስለሚሰሩ ኢትዮጵያውያን ሰራተኞች የስራ ስምሪት ደህንነት አጠባበቅ ቀልጣፋና ፍትሐዊ መሆኑን ማረጋገጥ | 1. ለሥራ ወደ ውጭ አገር የሚሄድ ሠራተኛ የሥራ ውል ለመ/ቤቱ ቀርቦ መጽደቅ አለበት፡፡ |
| | 2. ለማንኛውም ሥራ ወደ ውጭ አገር ለሚሄዱ ኢትዮጵያውያን አሰሪው ኢንሹራንስ ሊገባላቸው ይገባል፡፡ |
| | 3. አሰሪው ለሰራተኛው ኢንሹራንስ መግባቱን የሚያሣይ ማስረጃ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያቀርብ ይገባል፡፡ |
| | 4. ለሥራ ወደ ውጭ አገር የሚሄዱ ኢትዮጵያውያን ሰራተኞች የሚሄዱበት አገር የሥራ ፈቃድ ለማግኘታቸው በኤምባሲ የተረጋገጠ ማስረጃ ሊቀርብ ይገባል፡፡ |
| | 5. ለውጭ አገር ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች የመከታተያ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 6. በሥራ ቅጥር ወደ ውጭ አገር ሠራተኛ የሚልክ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ሠራተኛውን በሚልክበት አገር ቅርንጫፍ ቢሮ ወይም ተወካይ ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 7. በውጭ አገር የሚገኝ የግል አሰሪና ሰራተኛ ኤጀንሲ ወኪል በስራና ሰራተኛ አገናኝነት ላይ ለመሳተፍ የንግድ ምዝገባና የሥራ ፈቃድ እንዳለው ሊረጋገጥ ይገባል:: |
| | 8. የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ከውጭ አገር የሚያገኘውን የውጭ ምንዛሪ በአገር ውስጥ ባንክ ገቢ ለመደረጉ በየ3 ወሩ ለመ/ቤቱ በሪፖርት ማሳወቅ አለበት፡፡ |
| | 9. ለውጭ አገር ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፈቃድ ለመስጠት መስፈርት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 10. ለውጭ አገር ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ በወጣው መስፈርት መሰረት ፍቃድ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 11. ለስራ ወደ ውጭ ለሚወጡ ዜጎች የስራ ስምሪት በውሉ መሰረት መሆኑን የመከታተያ ስርአት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 12. ለስራ ወደ ውጭ ለሚወጡ ዜጎች የውጭ ሀገር የስራ ስምሪት በጸደቀው የሥራ ውል መሰረት መፈፀሙን በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 13. ወደ ውጭ ተቀጥረው የሄዱ ሰራተኞች ቀደም ሲል የተደረገ የሥራ ውል በአዲስ ለመተካት ወይም ለማሻሻል የሚያስችል የሠራተኛውን ስምምነት ሲያገኝ በኢት/ያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት አቅርቦ የማጸደቅና ለሚ/መ/ቤቱ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ |
| | 14. በውጭ አገር ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች እና ለሥራ ወደ ውጭ በወጡ ሠራተኞች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን አስመልክቶ ሰራተኛው የህግ ምክር አገልግሎት እንዲያገኝ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 15. ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽኖች ተግባራዊ የሚደረጉበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 16. ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽኖች በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት ተግባራዊ መደረጋቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 17. ለክልል ቢሮዎች የሥራ ሥምሪት አገልግሎት የማጠናከሪያ ሥልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 18. ለክልል ቢሮዎች የሥራ ሥምሪት አገልግሎት ማጠናከሪያ የሚሠጠው ሥልጠና ለተገቢው ሰልጣኝ ሊሆን ይገባል፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| | 19. | በውጭ ሀገር ለስራ ተሰማርተው የሚመለሱ ዜጎች የመቋቋሚያ ድጋፍ የሚደረግበት ስርዓት መዘርጋት አለበት፡፡ |
| | 20. | በተዘረጋው መስፈርት መሰረት ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ |
| | 21. | በውጭ ሀገር ለስራ ተሰማርተው የሚመለሱ ዜጎች የመቋቋሚያ ድጋፍ ለማድረግ ግልጽ የሆነ የመምረጫ መስፈርት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 22. | በሥራ ምክንያት ውጭ ቆይተው ወደ አገራቸው የሚመጡ ኢትዮጵያውያን ዝርዝር ተመዝግቦ ሊያዝ ይገባል፡፡ |
| | 23. | በውጭ ሀገር በስራ ተሰማርተው የሚመለሱ ዜጎች ያገኙትን ገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም ላይ ስልጠናና ግንዛቤ መስጠት ይገባል ፡፡ |
| | 24. | በውጭ ሀገር በስራ ተሰማርተው የሚመለሱ ዜጎች ተደራጅተው በጥቃቅንና አነስተኛ የስራ መስክ የሚሰማሩበት ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 25. | ከውጭ አገር ሥራ ሥምሪት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ አቤቱታዎችና ጥቆማዎች አፋጣኝ ምላሽ የሚያገኝበት ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| 2. በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር በስራ ተሰማርተው ለሚስሩ ዜጎች የስራ ስምሪት የተደራጀ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ | 26. | ከውጭ አገር በሚመጡ ሰራተኞች ለሚሰራ ሥራ የስራ ገቢያ መረጃ ስርዓትን ደረጃ በደረጃ በማጠናከር መረጃዎች ተሰብስበው ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ መደረግ አለበት |
| | 27. | የክልል ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች የሥራ ገበያ መረጃ በማሰባሰብ የሚያሳውቁበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 28. | ከውጭ አገር የሚመጡ የውጭ አገር ዜጎች ስለ ሚሰሯቸው የሥራ አይነቶች ከክልል የሚሰበሰቡ መረጃዎች ወቅታዊ ሊሆኑ ይገባል፡፡ |
| | 29. | ለህብረተሰቡ ስለውጭ አገር ስራ ስምሪት ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ ከጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 30. | የተሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ውጤታማነቱ ሊገመገም ይገባል፡፡ |
| | 31. | ለውጭ አገር የሥራ ሥምሪት የሚቀርቡ ኮንትራት ውሎች በውጭ አገር በሚገኝ የኢትየጵያ ኤምባሲ የተረጋገጠ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 32. | ለውጭ ሥራ ሥምሪት የተዘጋጀው የሥራ ውል በየዓመቱ ሊከለስ ይገባል፡፡ |
| 3. ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተቀጥረው ሰለሚሰሩ የውጭ አገር ዜጎች የፈቃድ አሰጣጥና የሥራ ስምሪት ቀልጣፋና ፍትሀዊ መሆኑን ማረጋገጥ | 33. | ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ አሰጣጥና አፈጻጸም የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 34. | ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ሲሰጥ ሥራው በኢትዮጵያ ባለሙያ አለመሸፈኑ ተረጋግጦ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 35. | ለውጭ አገር ዜጎች የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ ለሥራው ተገቢው ሙያ ያለው መሆኑን በማረጋገጥ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 36. | የውጭ አገር ዜጎች ተቀጥረው በሚሰሩበት ቦታ የሚተኩ ኢትዮጵያውያን እንዲሰለጥኑ ሊደረግ ይገባል ፡፡ |
| | 37. | የሚተኩ ኢትዮጵያውያን እንዲሰለጥኑ በማድረግ ሪፖርት ለመቅረቡ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 38. | ፈቃድ ሲታደስ ተተኪ ባለሙያ ሊያፈሩ ያልቻሉበትን ምክንያት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ |